# የሕዳሴ ግድብ ቦንድ ባህርያት አጭር መግለጫ

1. **የህዳሴ ግድብ ቦንድ ባህሪያት**

   ቦንድ ምንድን ነው ?

   1. ቦንድ መንግሥት ሙሉ ዋስትና የሚሰጠው ወለድ የሚገኝበት ተመልሶ የሚከፈል የብድር ሰነድ ነው።
   2. የህዳሴ ግድብ ቦንድ የኢትዮጵያ መንግሥት በአባይ ወንዝ ላይ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት የሚያስችል ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያስችል ለሽያጭ የቀረበ ቦንድ ነው።

2. **የቦንዱ ዓይነት**
   - ወለድ የሚከፈልበት ኩፖን ቦንድ
   - ወለድ የማይከፈልበት ኩፖን ቦንድ

   2.1. ቦንድ የሚሸጠው ለኢትዮጵያዊ፣ ትውልድ ኢትዮጵያዊ እና የአባይ ተፋሰስ ለሆኑት ለጐረቤት አገሮች ዜጐች /ኤርትራውያን/ ጭምር ነው።

   2.2. የቦንዱ ወለድ የሚከፈለው በየግማሽ ዓመቱ።

3. **ቦንዱ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች**

   3.1. ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው።

   3.2. ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ብድር መውሰድ ይቻላል።

   3.3. ለገዢው /ለደንበኞች/ ቋሚ የወለድ ገቢ ያስገኛል።

   3.4. የመንግስት ዋስትና ስላለው ከስጋት ነፃ ነው።

   3.5. ከመደበኛ ባንክ የቁጠባ ወለድ የተሻለ የወለድ ገቢ ያስገኛል።

   3.6. ለደንበኛው /ለገዢው/ ሕጋዊ ወራሾች ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ ይችላል።

4. **የቦንድ ዋጋ**

   4.1. ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ (minimum bond) በዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ 50 ሆኖ ባለ 100፣ 300፣ 500፣ 1,000፣ 3,000፣ 5,000 እና 10 ,000 ቦንዶችም ለገበያ ቀርበዋል።

   4.2. በተጨማሪነት ቅንስናሾችን ለማስተናገድ እንዲቻል በዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ ባለ 5 እና 10 ዋጋ ያላቸው ቦንዶችም ለሽያጭ ቀርበዋል። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የ55 ዶላር ቦንድ መግዛት ቢፈልግ አንድ ባለ 50 ዶላር ቦንድ እና ተጨማሪ ባለ 5 ዶላር ይሰጠዋል ማለት ነው።

   4.3. የቦንዱ ሽያጭ የሚከናወነው በዶላር፣ ፓውንድ ስተርሊንግ፣ ዩሮ፣ ስዊዝ ፍራንክ፣ ሪያል፣ ድርሃም፣ ስዊድሽ እና ኖርዌይ ክሮነር እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንድ በሚገበያይባቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ይሆናል።

5. **ቦንዱን ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፣**

   5.1. አቅመ አዳም/ሔዋን የደረሱ፣

   5.2. የኢትዮጵያ ፓስፖርት ያላቸው፣

   5.3. የኮሚኒቲ መታወቂያ የያዙ፣

   5.4. የትውልድ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ካርድ የያዙ፣

   5.5. የውጭ አገሮች ፓስፖርት የያዙት ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣

   5.6. የኢትዮጵያ ተወላጅነትን የሚገልፅ ማንኛውም ማስረጃ የያዙ፣

   5.7. የትራቭል ዶኩመንት የያዙ ኢትዮጵያዊያን፣

   5.8. ምንም ዓይነት ማስረጃ የሌላቸውና ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚችሉ፣

   5.9. አንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ (passport size) ማቅረብ ያስፈልጋል፣

6. **የቦንዱ የክፍያ ጊዜና ወለድ**

   6.1. የወለድ መጣኔ

   የሚከፈለው የወለድ መጣኔ የቦንዱን የክፍያ ጊዜ ያገናዘበ ሆኖ:-

   - 5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው ...... LIBOR+1.25 በመቶ
   - ከ6-7 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው ....... LIBOR+1.5 በመቶ
   - ከ8-10 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው ...... LIBOR+2.2.0 በመቶ ይሆናል።

7. **ከክፍያ ጊዜ በፊት ስለሚመለሱ ቦንዶች.**

ገዥዎች ቦንዱን ከክፍያ ጊዜ በፊት መመለስ ይችላሉ፣ በዚሁ መሠረት:

- ከ1-5 ዓመት የሆነ ቦንድ የገዙት ቦንዱን ከገዙበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 1 ዓመት ጠብቀው ገንዘቡን መውሰድ ይችላሉ::
- ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ቦንድ የገዙት ቦንዱን ከገዙበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 3 ዓመት ጠብቀው ገንዘቡን መውሰድ ይችላሉ፣

8. **ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች**

8.1. የክፍያውን ገንዘብ በስዊፍት /SWIFT/ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ

8.1.1. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ correspondent banks በኩል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ SWIFT ግንኙነት ካላቸው 40 ታላላቅ ባንኮች ጋር **/ከዌብሳይታችን ዋናውን ሰነድ ሡንጠረዥ፣ ይመልከቱ/**የ correspondent banking ግንኙነት አለው:: እነዚህ ባንኮች በብዙ ሀገራት ቅረንጫፎች በመሄድ በቀላሉ ገንዘቡን ማስተላለፍ ይችላል::

8.2. የክፍያውን ገንዘብ በኤምባሲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ፣

8.3. የክፍያውን ገንዘብ በብሉ ናይል አፍሪካን አርት የገንዘብ አስተላላፊ ኤጀንት /Money transfer Agent/ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ፣

8.4. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ውስጥ ከሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ክፍያውን መፈጸም፣

9. **የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ፣**

9.1. ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው በውጭ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልድ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ሃገር ዜጎች ነው:: ነገር ግን ቦንዱ በሀገር ውስጥ ገንዘብ እንዲከፈልለት ከፈለገ በሀገር ውስጥ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ማስተላለፍ ይችላል::

9.2. ቦንድ ገዥው ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን በጀርባው ላይ በመፈረም ብቻ በውርስና በስጦታ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፣ ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ወይንም ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ /Secondary Market/ ለሌላ ገዢ መሸጥ ይችላል::

10. **የህዳሴ ቦንድ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት፣**

10.1. የህዳሴ ቦንድን ለሌላ ሰው መግዛት ይቻላል:: ነገር ግን ቦንዱ ላይ ስሙ የሚፃፈው ቦንዱ የሚገዛለት ሰው ስም /የቦንዱ ባለቤት/ መሆን አለበት:: በሌላ ሰው ስም ቦንዱን የሚገዛው ሰው በቦንዱ ላይ "ስለ" ብሎ መፈረም ይችላል:: በየጊዜው የወለድ ክፍያ የሚፈፀመውና ዋናው ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው ግን ቦንድ ለተገዛለት ሰው ወይም ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው/ጣት ብቻ ነው::

10.2. ለአቅመ አዳም/ሔዋን ላልደረሱ ልጆች በወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው አማካኝነት በቦንዱ ላይ የልጁን/ቷን ስም በመፃፍና "ስለ" ብለው በመፈረም ቦንዱን መግዛት ይችላሉ:: ልጁ/ቷ 18 ዓመት እስኪሞላው/ት ድረስ ከቦንዱ የሚገኘው ጥቅም እንዲቀመጥ ወላጅ/አሳዳጊ ከፈለገ በዚሁ መሠረት ማስተናገድ ይቻላል::

11. **ለግድቡ ስጦታን በተመለተ**

11.1. ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ነፃ የገንዘብ ስጦታ ማበርከት ይቻላል፣

11.2. ስጦታውን የሚለግሰው ግለሰብ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ልክ ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጠዋል::

12. **ስለቦንዱ አገዛዝ ማብራሪያ ከፈለጉ**

12.1. በስልክ ቁጥር 02075897212 ደውለው መረጃ ማግኘት ይችላሉ::

12.2. እንዲሁም የኤምባሲውን ድረ-ገፅ WWW.ethioembassy.org.uk ይጐብኙ

**LIBOR**: London Interbank Offer Rate ማለት በለንደን የገንዘብ ገበያ ባንኮች በየዕለቱ እርስ በእርሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ መጣኔ ነው:: ይህ መጣኔ ብዙ ባንኮች የራሳቸውን የወለድ መጣኔ ለመወሰን እንደመነሻ የሚጠቀሙበት ነው:: የ LIBOR መጣኔን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገፅ ላይ መመልከት ይቻላል::